# ስለ የጦጣ ፈንጣጣ እውነታዎች

Maryland
DEPARTMENT OF HEALTH

## ምንድን ነው?

የጦጣ ፈንጣጣ በጦጣ ቫይረስ ከስንት አንዴ የሚከሰት ኢንፌክሽን ነው። የጦጣ ፈንጣጣ ሽፍታ ወይም ቁስሎች (ፖክስ)፣ አንዳንዴም በጉንፋን መሰል በሽታን ጨምሮ ሊያሳምምዎ ይችላል። ክትባት የጦጣ ፈንጣጣ ስርጭትን ለመከላከል ወሳኝ መሳሪያ ነው። ክትባቱ ከከባድ ሕመም፣ ሆስፒታል ከመተኛት እና ከሞት ሊከላከል ይችላል። ለተሻለ ጥበቃ ሁለቱንም ክትባት ይከተቡ። የጦጣ ፈንጣጣ ክትባት ለእርስዎ የሚመከር መሆኑን ለማወቅከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ያረጋግጡ ።

## እንዴት ነው የሚስፋፋው?

ቫይረሱ ወደ ማንኛውም ሰው በመቀራረብ፣ በግል ወይም በቆዳ-ለቆዳ ንክኪ ሊሰራጭ ይችላል፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፦



ከጦጣ ፈንጣጣ ሽፍታ፣ ቁስሎች ወይም ማሳከክ ጋር መነካካት



በጦጣ ፈንጣጣ የተያዘ ሰው ከተጠቀመባቸው ዕቃዎች፣ ጨርቆች (ልብስ፣ አልጋ ልብስ፣ ወይም ፎጣ) ጋር መነካካት



በጦጣ ፈንጣጣ የተያዘ ሰው በመተንፈሻ አካላት ጠብታ ወይም ምራቅ በኩል



ነፍሰ ጡር ሰዎች በእርግዝና ወቅት ቫይረሱን ወደ ፅንሱ ሊያስተላልፉ ይችላሉ

- እንደነዚህ ያሉ ግንኙነቶች በሚከተለው ወቅት ሊከሰቱ ይችላሉ፦
  - በማቀፍ፣ በመሳም፣ በመንካት፣ በማሸት
  - መቀራረብ፣ ወሲባዊ ግንኙነት
  - የጦጣ ፈንጣጣ ካለበት ሰው ጋር ረዘም ላለ ጊዜ ፊት ለፊት መገናኘት
  - በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት ጦጣ ፈንጣጣ ያለበት ሰው ይጠቀምባቸው የነበሩ ጨርቆችን እና እቃዎችን መንካት፣ እንደ አልጋ ልብስ፣ ፎጣ እና የወሲብ አሻንጉሊቶችን
- ቫይረሱ በፈሳሽ ወይም ከጦጣ ፈንጣጣ ቁስሎች ከሚመጣ በመግል ሊተላለፍ ይችላል። በወንድ የዘር ፈሳሽ ወይም በሴት ብልት ፈሳሾች ውስጥ መኖሩን እስካሁን አልታወቀም።

## ምልክቶቹ ምንድን ናቸው?

- ጦጣ ፈንጣጣ ሽፍታን ወይም ህመምን ያስከትላል። እንዲሁም ጉንፋን እንዳለብዎ እንዲሰማዎት ሊያደርግ ይችላል።
- የጉንፋን ምልክቶች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፦
  - ትኩሳት
  - ራስ ምታት
  - የጡንቻ ህመም እና የጀርባ ህመም
  - የጉሮሮ ማበጥ
  - ብርድ ብርድ ማለት
  - ድካም
- ሽፍታ ወይም ቁስሎች በእጆች፣ እግሮች፣ ደረት፣ ፊት፣ ብልት ወይም በአፍ ውስጥ ወይም በአፍ ላይ፣ በሴት ብልት፣ እና በፊንጢጣ ላይ ሊሆኑ ይችላሉ።
- ቁስሎቹ እንደ ብጉር ወይም ውሃ የቋጠሩ ሊመስሉ ይችላሉ፣ እና የሚያም ወይም የሚያሳክኩ ሊሆኑ ይችላሉ።
- ከመዳኑ በፊት፣ ማሳከክን ጨምሮ በተለያዩ ደረጃዎች ውስጥ ያልፋሉ።
- የጦጣ ፈንጣጣ ምልክቶች ከታዩበት ጊዜ አንስቶ ሁሉም ቁስሎች እስከሚድኑ እና አዲስ የቆዳ ሽፋን እስኪፈጠር ድረስ ሊተላለፍ ይችላል—ይህ ብዙ ሳምንታት ሊወስድ ይችላል።

## ምልክቶች ካለዎት ምን ማድረግ አለብዎት?

### አዲስ ወይም ያልታወቀ ሽፍታ፣ ቁስሎች፣ ወይም ሌሎች ምልክቶች ካለብዎ...

- የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ይመልከቱ። አቅራቢ ወይም የጤና መድን ከሌለዎት በአቅራቢያ የሚገኝ የጤና መመሪያ ለማግኘት health.maryland.gov/CSTIP/local ይጎብኙ።
- ለጦጣ ፈንጣጣ ምርመራ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ሲያገኙ፣ ይህ ቫይረስ በማህበረሰቡ ውስጥ ሊሰራጭ እንደሚችል ያስታውሷቸው።
- ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር እስከሚነጋገሩ ድረስ ከማንም ጋር አካላዊ ንክኪን ያስወግዱ።

### እርስዎ ወይም አጋርዎ የጦጣ ፈንጣጣ ካለብዎት...

- የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን የህክምና እና የመከላከያ ምክሮችን ይከተሉ።
- ሁሉም ቁስሎችዎ እስኪድኑ እና አዲስ የቆዳ ሽፋን እስኪፈጠር ድረስ ከማንም ጋር የቅርብ አካላዊ ንክኪ ያስወግዱ።

ይህ ሰነድ ባለፈው ኦገስት 17፣ 2022 ተሻሽሏል። ይህ ሰነድ የሚዘመነው አግባብነት ያላቸው ክለሳዎች ሲደረጉ ብቻ ነው።

ክለሳ 080424

የሜሪላንድ የጤና መምሪያ • የአባላዘር በሽታዎች መከላከል ማዕከል
201 W. Preston St., Baltimore, MD 21201 | health.maryland.gov/mpox